# የብሉይ ኪዳን ነቢያት



ትምህርት 3

ለጥቅምት 7/ 2019



«ማልደውም ተነሡ፥ ወደ
ቴቁሔም ምድረ በዳ ወጡ፤
ሲወጡም ኢዮሣፍጥ ቆመና፦
ይሁዳና በኢየሩሳሌም
የምትኖሩ ሆይ፥ ስሙኝ
በአምላካችሁ በእግዚአብሔር
እመኑ፥ ትጸኑማላችሁ፤
በነቢያቱም እመኑ፥ ነገሩም
ይሰላላችኋል አለ።»

(2 ዜና 20:20)

ከእግዚአብሔር መልዕክትን ተቀብለው ለሌሎች የሚያስተላልፉ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመናት ባለ ራዕዮች ወይም ነቢያት በመባል ይጠሩ ነበር (1 ሳሙ 9:9)።

የተሰወሩ ነገሮችን የማወቅና ወደፊት የሚሆነውን እንኳን የመረዳት ችሎታ ነበራቸው (1ሳሙ 9:6)፤ ነገር ግን ሥራቸው በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሰፊ ጉዳዮችን ያካተተ ነው። በእርግጥ ይህ ችሎታ የመጣው ከራሳቸው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው።

ደግሞም “ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራዕይ” የሚናገሩ ሀሰተኛ ነቢያትም ነበሩ (ኤር 23:16)።





- ለትንቢት አገልግሎት የተጠሩት እነማን ነበሩ?
- የነቢያት ባህሪ እንዴት ነበር?
- የነቢያት ሥራ ምንድን ነበር?
- የትንቢት ሥጦታ የነበራቸው ሴቶች እነማን ነበሩ?
- የሀሰተኛ ነቢያት ባህሪ እንዴት ነበር?

# ለትንቢት አገልግሎት የተጠሩት እነማን ነበሩ?

"ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥" (ያዕቆብ 5:17)

ብዙ ጊዜ ነቢያት "ኃያላን ሰዎች" ነበሩ የሚል ስህተትን ወደ ማመን ልንወድቅ እንችላለን። ሙሴ አፈ ኮልታፋ በመሆኑ ጥሪውን አልቀበልም ማለቱን እናስታውስ (ዘጸ 4:10)፣ ኢሳይያስም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ነኝ ብሎ ነበር (ኢሳ 6:5)፣ ኤርምያስ ደግሞ ለሥራው ገና ታናሽ ልጅ ነኝ ብሎ አስቦ ነበር (ኤር 1:6)።

ኤልያስ በንጉሥ አካብ አለመታዘዝ ምክንያት ታላቅ ረሃብ እንዲመጣ ቢያደርግም "እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ" (ያቆ 5:17)።











ታላቅ ተዓምር በሰራ ማግስት በንግሥት ኤልዛቤል የግድያ ዛቻ ልቡ በፍርሃት ርዶና ተሸንፎ ነበር (1 ነገ 19:2-4)።

እግዚአብሔር ነቢያቱን የሚመርጠው ፍጹማን ስለነበሩ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ታዲያ በእነርሱ ውስጥ ምን አይቶ ነው? ለእርሱ ያላቸውን ፍቅርና እርሱን ለመታዘዝ ያላቸውን ፈቃደኝነት ተመልክቶ ነው።



# የነቢያት ባህሪ እንዴት ነበር?

“ሚክያስም፡- ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር የሚነግረኝን እርሱን እናገራለሁ አለ።” (1 ነገሥት 22:14)





ወንዶችና ሴቶች ነቢያት የእግዚአብሔር ድምጽ እንደመሆናቸው ለጥሪያቸው የሚመጥን አገልግሎትን ለመስጠት ይተጉ ነበር (1 ሳሙ 12:3-4)። ሕዝቡም “የእግዚአብሔር ሰው” እና “የተከበረ ሰው” በማለት ይጠሯቸው ነበር (1ሳሙ 9:6)።

የነቢያቱን መልዕክት ሊቀበሉ የማይወዱ ሰዎች ይጠሏቸውና ያስፈራሯቸው ነበር (1 ነገ 22:8፣ 27)። ነገር ግን ምንም አይነት ግፊት ቢያጋጥማቸውም መልዕክታቸውን በታማኝነት ያስተላልፉ ነበር።

ነቢዩ ሚክያስ በአንድ ወቅት በሁለት ነገሥታት ፊት 400 ነቢያት መልካም ነገርን በሚተነብዩበትና እርሱም ተመሳስሎ እንዲናገር የንጉሡ ጠባቂ እርሱን በሚመክርበት ሁኔታ ውስጥ ቆሞ ነበር (1 ነገ 22:10-13)። ቢሆንም ግን በጽናት በመቆም እግዚአብሔር ከገለጠለት ውጪ ምንም ላይናገር ቆርጦ ነበር (1 ነገ 22:14)።

ነቢያት ፍጹማን ባይሆኑም የጸሎት ሰዎች፣ ለቃሉ ታማኝ የሆኑ፣ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያገለግሉ ሰዎች ነበሩ (1ሳሙ 12:23፣ ኤር 42:4)።





# የነቢያት ሥራ ምንድን ነበር?

“በእስራኤልም ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የናሜሲን ልጅ ኢዩን ቅባው፤ በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልምሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው፤” (1 ነገሥት 19:16)

ነቢያት እነዚህንና ሌሎችንም ሥራዎች ይሰሩ ነበር:









## በነገሥታት ዙሪያ

- ነገሥታትን ይቀቧቸው ነበር (1 ነገ 19:16)
- መልካም ሲሰሩ ያበረታቷቸው ነበር (2ዜና 15:8)
- ሲሳሳቱ ደግሞ ሊያቃኗቸው በፊታቸው ይቆሙ ነበረ (1 ነገ 21:20)

## በካህናት ዙሪያ

- ሲሳሳቱ ያስተካክሏቸው ነበር (ሚል 2:1-2)

## በሕዝቡ ዙሪያ

- በእግዚአብሔር መንገድ ይመሯቸው ነበር (ሚክ 6:8)
- ኃጥያታቸው ያሳዩአቸው ነበር (ኢሳ 58:1)
- ወደ ንስሃ ይጠሯቸው ነበር (ሕዝ 18:32)

## ለእኛ

- መልዕክቶቻቸውን ለእኛ በጽሁፍ አስቀምጠውልን አልፈዋል (2ዜና 13:22)

# የትንቢት ሥጦታ የነበራቸው ሴቶች እነማን ነበሩ?

"በዚያ ጊዜም ነቢይቱ የለፊዶት ሚስት ዲቦራ በእስራኤል ላይ ትፈርድ ነበረች።" (መሳፍንት 4:4)

ብሉይ ኪዳን አምስት ሴት ነቢያትን ይጠቅስልናል። ከእነርሱ አንዷ ኖዓድያ ሀሰተኛ ነቢይ ነበረች (ነህ 6:14)። ሌላኛዋ ነቢዩት ደግሞ የኢሳይያስ ሚስት ስትሆን ነቢይ ተብላ የተጠራችበት ምክንያቱ የትንቢት ስጦታው ስለነበራት በመሆኑ ወይም የነቢይ ሚስት ስለነበረች እንደሆነ አይታወቅም (ኢሳ 8:3)።









**ነቢዩቱ ማርያም.** እስራኤል የቀይ ባህርን ከተሻገሩ በኋላ ሴቶቹን በመዝሙር መርታ ነበር። በበረሃ ቆይታቸውም ሕዝቡን በማምራት ወንድሞቿን ስትረዳ ነበር
(ዘጸ 15:20፣ ሚክ 6:4)።

**ነቢዩቱ ዲቦራ.** የነብይነትና የመሳፍንትነት ድርብ ማዕረግን ስትይዝ ከሲሣራ ጋር በነበረው ውጊያ ሕዝቡን ከባርቅ ጋር በመሆን መርታ ነበር። ጦርነቱን ካሸነፉ በኋላ ትንቢታዊ የምሥጋናን መዝሙር ተቀኝታ ነበር (መሳ 4:4-9; 5:1)።

**ነቢዩቱ ሕልዳና.** ንጉሡ ኢዮስያስ ጠፍቶ ስለተገኘው የሕጉ መጽሐፍ ነቢዩቱን አማክሯት ነበር። የንጉሡን ጥያቄ ከመመለስም በተጨማሪ የሚያበረታቱ ቃላትን ተናግራው ነበር
(2 ነገ 22:14-20)።

# የሀሰተኛ ነቢያት ባህሪ እንዴት ነበር?

“እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፦ ነቢያቱ ውሸት በስሜ ትንቢት ይናገራሉ፤ አላክኋቸውም፥ አላዘዝኋቸውም፥ አልተናገርኋቸውም፤ የውሸቱን ራእይ ምዋርትንም ከንቱንም ነገር የልባቸውንም ሽንገላ ይሰብኩላችኋል።” (ኤርምያስ 14፡14)



ትንቢትን የተናገሩ ሁሉ ከእግዚአብሔር መልዕክትን የተቀበሉ ነበሩ ማለት አይቻልም (ኤር 14:14)። መልዕክታቸው ምንድን ነበር? ያስተላለፉትስ ለምን ነበር?

- ከገዛ ልባቸው የሚተነብዩ ነበሩ (ሕዝ 13:2፣ 17)
- ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን ይናገሩ ነበር (ሕዝ 13:16)
- ኃጥያትን ተቃውመው  አይናገሩም ነበር (ሕዝ 13:22)
- የግል ጥቅማቸውን የሚፈልጉ ነበሩ (ሕዝ 13:19)

እውነት አለመሆኑን እያወቁ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያሉ ለምን ይናገራሉ? እራስን ማታለል ነው? ዝናን ፍለጋ ወይም ገንዘብን ለማግኘት ነው?



ስለ ሀሰተኛ ነቢያት የሚያሳዝነው ነገር የሚሰሟቸውና የሚከተሏቸው ሰዎች መኖራቸው ነው። ምንም ጥረት የማያስፈልገውና ህሊናቸውን የሚቆረቁር ስላልሆነ ሰሚዎቹ የሚሰሙትን ነገር ይወዱታል። ነገር ግን ይህን መንገድ መከተል መጨረሻው ሞት ነው።

እውነተኛ ነቢይ ሁልጊዜ ስለ ኃጥያት አደጋ የሚያስጠነቅቅ እና ሰዎችን ምንም ቢያስከትልባቸውም ታማኝ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ነው።

“የትኞቹም ሐዋርያትና ነቢያት ኃጥያት የለሽ ነን አላሉም። ለእግዚአብሔር በቅርበት የኖሩ፤ እያወቁ ስህተትን ከመስራት ህይወትን መሰዋት የሚመርጡና እግዚአብሔር መለኮታዊ ብርሃንንና ኃይልን በመስጠት ያከበራቸው ሰዎች ኃጥያተኛ ተፈጥሮ እንዳላቸው ተናዝዘው ነበር። በስጋ ላይ ምንም አይነት መተማመኛን አላስቀመጡም፤ የራሴ ብለው የሚመኩበትም ጽድቅ አልነበራቸውም፤ ነገር ግን በክርስቶስ ጽድቅ ሙሉ በሙሉ ተማምነው ነበር”

EGW (The Acts of the Apostles, p. 561)

# አባሪ: የኤለን ጂ. ኋይት ትንቢታዊ ጥሪ

ኤለን የመጀመሪያዋን ራዕይ ከተመለከተች በኋላ ይህን የትንቢት አገልግሎት ለመፈጸም በቂ ዝግጅት እንደሌላት ተሰምቷት ነበር። ይህች የ 17 ዓመት ልጅ በነበራት አስቸጋሪ የጤና ሁኔታና ውሱን የትምህርት ደረጃ ጥሪዋን ለመወጣት እንዳልተገባችና ብቁ እንዳልሆነች ተሰምቷት ነበር።




ራዕዩን ካየች ከአንድ ሳምንት በኋላ ልትጋፈጠው ስላላት ተግዳሮቶች የሚያስጠነቅቅ ሌላ ራዕይን አየች። ከብዙ ጸሎት በኋላና አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ካበረታቷት በኋላ በስተመጨረሻ ኤለን ጥሪዋን ልትቀበለው ቻላለች።

ከሃያ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ብዙ ራዕዮችን ከተቀበለች በኋላ በባሏ ጄምስ ኋይት እገዛ በይፋ በ1863 የተቋቋመውን የ7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያንን መሰረት ለማስያዝ ትልቅ ድርሻ ተወጥታለች።




የእርሷ አገልግሎት የአድቬንቲስትን የጤና እና የትምህርት ተቋሞች ለማቋቋም ትልቅ ሚና የነበረው ሲሆን መለኮታዊ መገለጥ ያለባቸውና መለኮታዊ ምሪትን ዛሬም በዓለም ዙሪያ የሚያስተላልፉ ወደ 100,000 ገጾች የሚጠጉ ጽሁፎችን ትታ አልፋለች።

